መልእክት ሦስት

**የአንዱ አዲሱ ሰው ቅንብር—**
**ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ ባሕልን መተካቱ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ቆላ. 1:15-18፣ 27፤ 2:9-10፣ 16-18፤ 3:4፣ 10-11

I. **ወደ ቆላስይስ መጽሐፍ ጥልቀቶች ውስጥ ከገባን፣ ጳውሎስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከተሰወረው ከባሕል ጉዳይ ጋር ተጋድሎ እያደረገ እንዳለ እናያለን፦**

ሀ. ጳውሎስ በቆላስይስ 3፡11 *አረማዊ* የሚለውን ቃል መጠቀሙ ይህ መልእክት ከባሕል ጋር ተጋድሎ እንደሚያደርግ ጠንካራ ማመላከቻ ነው።

ለ. ባሕል ለመኖር እና ማንነታችንን ለመጠበቅ እኛ ያዳበርነው ስልታዊ ዘዴ ነው—ዘፍ. 4፡16-22፦

1. ባሕል ሁሉም ሰው ሆን ብሎ ሳይሆን የሚኖረው ኑሮ ነው—ኤፌ. 2:2-3፤ 4:17።
2. በዓለም ሁሉ ያሉ ሰዎች በባሕላቸው ተጽእኖ ሥር ናቸው።

ሐ. ባሕል በቆላስይስ ባሉት ቅዱሳን ላይ ጠንካራ ተጽዕኖ እንዳሳደረባቸው ሁሉ፣ ዛሬም ባሕል በእኛ ላይ ጠንካራ ተጽዕኖ ያሳድርብናል—ቆላ. 2:8-10፣ 16-18፦

1. ሳናውቀው፣ ወደ ውስጡ በተወለድንበት ባሕል ተጽዕኖ ሥር ነን፤ የዚህም ባሕል ንጥረ-ነገሮች የማንነታችን ክፍል ናቸው—ገላ. 4:3፣ 9፤ ቆላ. 2:8፣ 20።
2. ወደ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ስንመጣ፣ ባሕላችንን ከእኛ ጋር ይዘነው መጥተናል፣ ይህም ባሕል የክርስቶስ ድሰታችንን እና የቤተ ክርስቲያን ሕይወታችንን ያመነምናል።
3. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ያለው ልዩና-ብቸኛው ንጥረ-ነገር የሆነው ክርስቶስ እጅግ በጣም ሰፊ በሆነ መጠን በባሕል ተተክቷል—ቁ. 8፤ 3:11፦
   ሀ. በተወሰነ መጠን በማወቅ እና ባለማወቅ፣ ሁላችንም ባሕላችንን እንደ ውድ መዝገብ እንቆጥረዋለን ባለን ልዩ በሆነው ባሕላዊ የኋላ ታሪካችን ላይም ከፍ ያለ ዋጋ እናስቀምጣለን።
   ለ. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ክርስቶስ ከምንም ነገር በላይ በባሕል ተተክቷል—ቁ. 11።

II. **የቆላስይስ መጽሐፍ ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ሁሉን ነገር እንደ ሆነ ይገልጣል—1:15-18፣ 27፦**

ሀ. ይህ ድንቅ የሆነው ክርስቶስ ለእኛ ሁሉን ነገር የመሆኑ የጠራ ራእይ ያስፈልገናል።

ለ. እንደዚህ ያለው ራእይ ባሕል በክርስቶስ ልምምድ ላይ እና በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ላይ ያለውን ተጽዕኖ ሕልውናውን ያሳጣዋል፣ በባሕላችን የዳበርን እና የሠለጠንን ሰዎች ከመሆን ይልቅ በክርስቶስ የተያዝን፣ የእርሱ የተደረግን እና ፈጽመን የተሞላን ሰዎች እንሆናለን—3:11።

III. **ፊተኛ ስፍራ ያለው፣ ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ ሕይወታችን እና የአንዱ አዲሱ ሰው ልዩና ብቸኛ ቅንብር ነው—ቁ. 4፣ 10-11፦**

ሀ. አንዱ አዲሱ ሰው የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ቅንብር ክርስቶስ እና ክርስቶስ ብቻ ነው፤ የቤተ ክርስቲያን ይዘት ሁሉን-ካካተተው፣ ሁሉን-ደረስ ከሆነው ክርስቶስ ውጭ ሌላ ምንም ነገር አይደለም—1:15-18፤ 2:9-10።

ለ. እንደ ሕይወታችን እና የአንዱ አዲሱ ሰው ቅንብር፣ ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ ባሕላችንን በራሱ ይተካዋል—3:11።

ሐ. ክርስቶስን እንደ ዕድል-ፈንታችን የመደሰታችን ውጤቱ እንደ የአንዱ አዲሱ ሰው ይዘት እና ቅንብር እርሱን መለማመዳችን ነው፣ በመጨረሻም፣ የምንደሰተው ክርስቶስ የአዲሱ ሰው ቅንብር ይሆናል—1:12፤ 3:11።

መ. በቆላስይስ 3፡11 *መሠረት*፣ በአዲሱ ሰው ውስጥ ልዩ ልዩ የባሕል ልዩነቶች ሕልውናቸውን እንደያዙ የመቀጠል ምንም እድል-ፈንታ ሊኖራቸው አይችልም፦

1. በአንዱ አዲሱ ሰው ውስጥ ምንም የባሕል ልዩነቶች የሉም፣ ምክንያቱም የአዲሱ ሰው ሁሉም ክፍሎች በክርስቶስ ተቀናብረዋልና—ቁ. 11።
2. አዲሱ ሰው በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ ለክልላዊ፣ ለባሕላዊ ወይም ለብሔራዊ ልዩነቶች ምንም ክፍል የለም፣ ለየትኛውም ዘር፣ ዜግነት፣ ባሕል ወይም ማኅበራዊ ደረጃ ምንም ስፍራ የለም።

ሠ. ክርስቶስ የአዲሱ ሰው ልዩና ብቸኛ ቅንብር ስለሆነ፣ የዚህ አዲስ ሰው ክፍል በሆኑት አማኞች መካከል ልዩነቶች መኖር የለባቸውም፣ በአብያተ ክርስቲያናትም መካከል ልዩነቶች መኖር የለባቸውም—1 ቆሮ. 4:17፤ ራእ. 1:12፣ 20፤ 22:16።

## IV. እንደ የአዲሱ ሰው ቅንብር፣ ክርስቶስ ሁሉን ነው፣ በሁሉም ውስጥ ነው፤ ክርስቶስ ብልቶችን ሁሉ ነው፣ በብልቶች ሁሉ ውስጥም ነው—ቆላ. 3:11፦

ሀ. አዲሱ ሰው በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ ክርስቶስ ሁሉንም ሰው ነው፣ በሁሉም ሰው ውስጥ ነው—1:27፤ 3:11።

ለ. በአንድ በኩል፣ በአዲሱ ሰው ውስጥ ለፍጥረታዊው ሰው ምንም ክፍል የለም፣ ምክንያቱም ክርስቶስ ሁሉንም ብልቶች ነውና።

ሐ. በሌላ በኩል፣ ክርስቶስ በሁሉም ውስጥ የመሆኑ ሐቅ ብልቶቹ ሕልውናቸውን እንደያዙ የመቀጠላቸውን ሐቅ ያመለክታል፣ ይህም ያለ ክርስቶስ ሳይሆን ነገር ግን ክርስቶስ በውስጣቸው እንዳደረባቸው ሰዎች ነው—1:27።

መ. ክርስቶስን እንደ ሕይወታችን እና ቅንብራችን ስንወስድ፣ በውስጥ ጥልቀታችን ከክርስቶስ ጋር አንድ እንደ ሆንን እና ክርስቶስ እኛን እንደ ሆነ የዚህ ስሜት-ግንዛቤው አለን፣ በተመሳሳይ ጊዜ፣ እንደውም ክርስቶስ በውስጣችን እንዳለ ከዚህ የጠለቀ የስሜት ግንዛቤ አለን—3:4።

ሠ. አዲሱ ሰው በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ ክርስቶስ ሁሉን ነገር ነው፤ ይህ የሚያመለክተው አማኞች ሁሉ የግድ በክርስቶስ መቀናበር እንዳለባቸው ነው—1:15-18፤ 2:16-17፤ 3:4፣ 10-11፦

1. በክርስቶስ መሰረግ፣ በክርስቶስ ፈጽሞ መሞላት፣ እና ሕይወታዊ በሆነ መንገድ ወደ ማንነታችን ውስጥ የተሠራው ክርስቶስ ያለን መሆን አለብን—ገላ. 4:19፤ ኤፌ. 3:17።
2. በመጨረሻም፣ በክርስቶስ እንተካለን፣ ከዚያም በእውነታ፣ ክርስቶስ ሁሉን እና በሁሉም ይሆናል፤ የአዲሱ ሰው ሁሉንም ክፍል ይሆናል—ቆላ. 3:11።

ረ. አዲሱ ሰው ፍጥረታዊ ልዩነቶች ሁሉ እስኪወገዱ እና ሁሉም ሰው በክርስቶስ እስኪቀናበር ድረስ ክርስቶስ በሁሉም ቅዱሳን ውስጥ እኛን መስረጉ እና እኛን መተካቱ ነው—ገላ. 4:19፤ ኤፌ. 3:17፤ ቆላ. 1:27።

ሰ. ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ ራእይ በቂ ከሆነ የክርስቶስ ልምምድ ጋር ሲኖረን አንዱ አዲሱ ሰው በተግባራዊ መንገድ በመካከላችን ይገለጣል፣ የአዲሱንም ሰው ሕይወት እንገነዘባለን—3:10-17፤ ፊሊሞ. 10-16።

ሸ. ክርስቶስ የቅዱሳን ሁሉ ኑሮ ከሆነ፣ ያኔ እርሱ ብቻ በአዲሱ ሰው ውስጥ ይሆናል፣ ቅዱሳንም ሁሉ ዜግነታቸው ምንም ቢሆን ክርስቶስን ይኖራሉ፤ ከዚያም እውነተኛ እና ተግባራዊ በሆነ መንገድ ክርስቶስ የአዲሱን ሰው ብልቶችን ሁሉ ይሆናል—ቆላ. 3:11፤ ፊልጵ. 1:21።

## V. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የአንዱ አዲሱ ሰው የመጨረሻ መጠናቀቅ ትሆናለች—ኤፌ. 2:15-16፤ 4:24፤ ቆላ. 3:10-11፤ ራእ. 21:2፣ 9-10፦

ሀ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ስንሆን፣ የአጽናፍ-ዓለማዊውን የአንዱን አዲስ ሰው ሕይወት እንደሰታለን።

ለ. ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ ባሕላችንን እንዲተካ፣ በራሱ እንዲያቀናብረን እና በእውነታና በተግባራዊ መንገድ የአንዱ አዲሱ ሰው ክፍል እንዲያደርገን በመፍቀድ ዛሬ የዚህ ድሰታ ቅድመ-ቅምሻ ሊኖረን ይችላል—ቆላ. 1:27፤ 2:10፤ 3:4፣ 10-11።

© 2020 Living Stream Ministry